የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

Ethiopian People's Congress for United Struggle (Congress)

www.derbiaber.com consult4Eth@gmail.com

# የጉባኤው ጠቅላላ ሂደትና የተላለፉ የጋራ ውሳኔዎች ሪፖርት

የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ ለአንድነት ግንባር ምሥረታ ለሃያ ሁለት ወራት ያህል ሲያደርግ የቆየውን ዝግጅትና ውይይት በተግባር ለመተርጎም በካናዳ ዋና ከተማ በኦታዋ ውስጥ ከግንቦት 10 ቀን እስከ ግንቦት 13 ቀን 2004 ዓ.ም.(18-21 ሜይ 2012)ድረስ ጉባኤ አካሂዶ ሸንጎ መመሥረቱ በተለያዩ የዜና አውታሮች ተገልጿል።

ስለጠቅላላው ሂደት በሸንጎው በኩል አጠር ያለ ሪፖርት ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘው ይህን አጭር ዘገባ ያቀርባል።
ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም. (18-05-2012) የእንግዶች መቀበያ፣መመዝገቢያና የማረፊያ ቦታ ድልድል፣እንዲሁም የውይይቱ ሰነዶች የታደሉበት፣በምሽቱም የእራት ግብዣና የመተዋወቂያ ፕሮግራሞች የተከናወኑበት ቀን ነበር።

በማግስቱ ቅዳሜ ግንቦት 11 ቀን(19-05-2012)ከቁርስ በኋላ በ08.30 ስብሰባው በይፋ ተከፈተ፤በኦታዋ የሚኖሩት የጉባኤ አዘጋጁ ኮሚቴ አባላት ተወካይ “እንኳን ደህና መጣችሁ” በማለት ንግግር አደረጉ ከዚያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተወካይ የሆኑት ሊቀካህናት ምሳሌ እንግዳና በኢትዮጵያ የሙስሊም ሃይማኖት ተወካይ ስም–አቶ ሙሃመድ አህመድ ጀሚል የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘርና ሃይማኖት ሳይለየው አብሮ የኖረ፣ በጋብቻ የተሳሰረና የተዋለደ በአንድ አገር ልጅነት መንፈስ እጅ ለእጅ ተያይዞ ክፉና ደጉን አብሮ የተካፈለ መሆኑን በማውሳት፣አንድነቱ ሳይናጋ እንዲኖር ያላቸውን እምነትና ቁርጠኝነት የገለጹ ሲሆን መንግሥት የሚከተለውን በሁለቱ እምነቶች ላይ የከፋፍለህና አጣልተህ ግዛ ፖሊሲ በማውገዝ አብሮ መቆም እንደሚያስፈልግ አሳሰቡ። የጉባኤው ተሳታፊ ድርጅቶችና ግለሰቦች የግልና የቡድን ፍላጎታቸውን ወደ ጎን ትተው አገር በማዳኑ ተግባር ላይ እንዲያተኩሩና የመጣውን የጋራ ችግር በህብረት እንዲቋቋሙት አደራ በማለት ጉባኤው የመግባባትና፣ የፍቅር መንፈስ የሰፈነበት እንዲሆን፣ ለስኬትም ቁርጠኛነትና በአቋም መጽናትን የሚጠይቅ መሆኑን ፣ ፍርሃትና መከዳዳት በፈጣሪም የሚያስጠይቅ መሆኑን፣ ከሁለቱም ቅዱስ መጽሃፍት ምሳሌዎችን በመጥቀስ ምክር በመለገስ ጉባኤው የተሳካ እንዲሆን በመባረክና በመመረቅ በጸሎት ደምድመዋል።
ጉባኤውን የሚመሩ ሁለት ሊቀመንበሮች፣ ሁለት ጸሃፊዎችና ሁለት የጉባኤ ቃል አቀባዮች ከተመረጡ በኋላ ለመገኘት ካልቻሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች የተላኩ የደብዳቤና የቪዲዮ የድጋፍ መልእክቶች ቀረቡ። በስብሰባውም ላይ የተገኙት ድርጅቶች የየበኩላቸውን ስለጉባኤው መሳካት ያላቸውን ሙሉ ፍላጎትና እምነት በየተራ ገለጹ።

በመክፈቻው በዓል ላይ ብቻ ለመገኘት የተጋበዙት እንግዶች ከተሰናበቱ በኋላ የጉባኤው ተሳታፊዎችና ለታዛቢነት እንዲቀመጡ የተፈቀደላቸው ግለሰቦች የተገኙበት ጉባኤ ወደ ውይይቱ አጀንዳ አመራ።

በመጀመሪያው የውይይት አጀንዳ የቀረበው የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታን የሚመረምረው ሰነድ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የህብረት አስፈላጊነትን በሚተነትነው እርዕስ ላይ ነበር።በነዚህ አጀንዳ ነጥቦች ላይ በቀረበው ሰነድ ላይ ሙል መግባባትና ስምምነት ስለነበረ ብዙ ውይይት አልተደረገበትም ።የጊዜውን ማጠር ከግምት ውስጥ በማስገባት አከራካሪ ሊሆን ይችላል ወደሚለው ተከታይ እርዕስ እንዲያመራ ሃሳብ በመቅረቡ የቀድሞ ህብረቶችና ተመክሮዎች በሚለው የአጀንዳ ነጥብ ላይ ውይይቱ ተካሄደ። ብዙ የሃሳብ ልውውጥና አስተያየቶች ቀረቡ። ያለፉት ህብረቶች ጠንካራና ደካማ ጎን እንደነበራቸው፣የጠንካራ ጎናቸው ዋናው ገጽ በጠላትነት ሲተያዩ የነበሩት ለጊዜውም ቢሆን ተቀራርበው ለመወያየት መቻላቸውና በተግባር ማሳየታቸው ነበር። ያም ሆኖ ግን ደካማ ጎናቸው ከጥንካሪያቸው ይበልጥ ጎልቶ ይታይ እንደነበር ተብራርቶ ቀረበ። ለውድቀት ከዳረጋቸው ደካማ ጎን ውስጥ ጎልተው የታዩት፣የሚከተሉት ነበሩ። አለመተማመን፣ መጠራጠር፣ የጠራ የጋራ ዓላማ አለመነደፍ፣ የግልና የድርጅት ጥቅም ከአገር ጥቅም በላይ መታየቱ፣ በቁርጠኝነት ለዓላማ ለመቆም አለመቻል፣ መወላወልና በሥልጣን ላይ ያለውን ቡድን በሚገባ አለማወቅ፣ አንዱ አንዱን ገርስሶ የበላይ ለመሆን ጥረት ማድረግ፣ ከሕዝቡ ይልቅ ለውጭ ሃይሎች ጆሮና ልብን መክፈት፣ የነሱን ቡራኬ ለማግኘት መወዳደርና መሻማት፣ ችግርና ልዩነት ሲፈጠር ለማስወገድ የሚችል አካል አለመኖር,...ወዘተ የነበሩ ድክመቶች እንደሆኑ ተብራራ።

እነዚህን ድክመቶች እንደ ውድቀት ተመክሮዎች በመውሰድ ለወደፊቱ የተሻለ ህብረት ለመፍጠር እንደሚረዱና ድክመቶች እንዳይደገሙ የሚረዱ ሆነው ተገኝተዋል፡ስለሆነም የአሁኑ ለመፍጠር የታሰበው ህብረት ዓላማና ግቡን በግልጽ ያስቀመጠ፣ ወዳጅና ጠላቱን የለየ፣ ችግር ቢገጥመውና አለመግባባት ቢፈጠር ቅራኔው ከማደጉና ህብረቱ አደጋ ውስጥ ከመግባቱ በፊት የሚከላከልበት መሣሪያ እንዲኖረው ማስፈለጉ ታምኖበታል።

አምስት የህብረቱ መሰባሰቢያ የጋራ ነጥቦችን እንደዓላማ በማድረግ በዚያ ዙሪያ ሊሰበሰቡ የሚችሉትን ሃይሎች ድርጅቶችና ግለሰቦች የሚያደርገውን ጥሪ በቀጣይነት እንዲያስተላልፍ ጉባኤው ተቀብሏል።(ዝርዝሩን በተደጋጋሚ ያወጣቸውን የጥሪ መልእክቶች መመልከት ይረዳል) ዘላቂ ራዕዩ ሕዝባዊ ሥልጣን ሊሰረጽበት የሚችል ሕገመንግሥታዊ ሥርዓት ማቆም ነው።ለዚያም ጉዞ እንደ ድልድይ ሆኖ የሚረዳ የሽግግር መንግሥት ወደፊት ማቋቋም እንደሚገባ ታምኖበታል።ይህም አካል የሚመሰረተው በወቅቱ በሚደረግ ሁሉን ዓቀፍ በሆነ የጋራ ጉባዔ አማካኝነት ሲሆን የአገልግሎት ዕድሜውም ከሁለት ዓመት እንዳይበልጥ ስምምነት ላይ ተደርሷል።

በዚህ የጋራ ግንባር ውስጥ ለመሳተፍ የሚችሉት
1ኛ/የሰብሰቡን አምስት ዓላማዎች የተቀበሉ ማለትም የሕዝቡን ልዑላዊነትና የአገሪቱን የግዛት አንድነት ፣ በሰብዓዊ መብት መከበር፣ በዜጋ እኩልነትና በሕግ የበላይነት፣ ብሎም በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈንና በሥልጣን ላይ ያለው የህወሃት/ኢህአዴግ ሥርዓት የአፈናና የጭቆና ሥርዓት በመሆኑ መወገድ እንዳለበት ማመንና ለዚያም መታገል፣

2ኛ/ለውጭ ሃይሎች/አገሮች/ጥቅም ተገዥና አገልጋይ ያልሆነ፣ የአገሩንና የሕዝቡን ጥቅም አሳልፎ ላለመስጠት ቁርጠኛ ሆኖ መገኘት፣

እነዚህ በዋናነት የሚቀመጡ መስፈርቶች ሲሆኑ በአሠራር ደረጃ ሊከሰቱ የሚችሉትን የህብረት እንቅፋቶች ፣ማለትም:
አንድነትን ብቻ እያከረሩ ለብሔር እኩልነትና አንድነት የሚታገሉትን ዴሞክራቲክ ሃይሎች ለማራቅ የሚደረግን ሙከራ መከላከል በአንጻሩም የብሄርን መብት ብቻ ቅድሚያ በመስጠትና በማክረር የአንድነትን ስሜት የሚያላላና የሚቃወም ድርጊትን መታገል እንደሚያስፈልግ ጉባኤው አምኖበታል።

በተከሰቱ ችግሮችና ሂደቶች ላይ የጠለቀ ውይይት ተካሂዶ የመፍትሄ ሃሳቦችም ተደርድረው ከታዩና ከተመረመሩ በኋላ ለችግሩ መፍትሄ መሣሪያ የሚሆን ጠንካራ ግንባር መመስረት ብቻ እንደሆነ ሙሉ በሙሉ ታምኖበታል። የሚፈጠረውም የአንድነት ግንባር፣ ጉባኤው ተቀብሎ ያሳለፋቸውን ዓላማዎችና ራዕይ ይዞ የሚጓዝ ሁሉም የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት፣ የሲቪክ ማህበራትንና ግለሰቦችን ያቀፈ እንዲሆን ተወስኖ በስብሰባው የሁለተኛ ቀን ቅዳሜ ግንቦት 11 ቀን 2004 ዓ.ም. (19-05-2012) ከምሽቱ 20.30 ላይ በሙሉ ድምጽ ህብረቱ ተመሠረተ። ስሙም "የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ" በአጭር አጠራር "ሸንጎ" እንዲባል ተወሰነ። አርማውም በቡቃያ ሃረግ /ዘንባባ/የተከበበ በሕዝቦች እጅ የተደገፈ ጋሻ መደቡ የኢትዮጵያ ባንዲራ ፣ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ እንዲሆን (በቀጣዩ–ምክር ቤት ስብሰባ) ተወሰነ።

ምክር ቤት አወቃቀር በተመለከተ፣ ከፖለቲካ ድርጅቶችና ከሲቪክ ማህበራት ከእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ተወካዮች ፣ ከግለሰቦች መካከል ደግሞ 5 ሰዎች እንዲቀላቀሉ በመወሰኑ በጠቅላላው በቦታው ከተገኙት ውስጥ 19 ሰዎች የምክር ቤት አባላት ሆነዋል። ያልተገኙትና ገና ወደፊት ተወካዮቻቸውን ለመሰየም ቃል የገቡት ሲጨመሩ የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር ከፍ እንደሚል ታምኖበታል። በድምጽ አሰጣጥም ላይ የሚኖራቸው ድርሻ የፖለቲካ ድርጅቶች 40%፣ የሲቪክ ማህበራት 40%፣ የግለሰቦች 20% እንዲሆን ስምምነት ላይ ተደርሷል። ይህ አዲስ አይነት አሠራር እንደቀድሞ ጊዜ የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ የነበራቸውን ሃይልና የመወሰን መብት ሚዛናዊ ክፍፍል በማድረግ፣ ሌላው የአገሪቱ ዜጋ በውሳኔ ላይ ድምጽ የመስጠት መብቱ እንዲከበርለት የሚያደርግ አዲስ ለውጥ ነው።

ምክር ቤቱ ከተመሠረተ በኋላ የሥራ አመራርና ዘርፎችን በተመለከተ ውይይት አካሂዶ ለአንድ ዓመት ማለትም እስከሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ ድረስ የሚያገለግሉ ሥራ አስፈጻሚ አባላትን መርጧል።
ዶ/ር ኤርምያስ ዓለሙ - ሊቀመንበር፣ ፕሮፌሶር አቻምየለህ ደበላ - ም/ሊቀመንበር፣ አቶ ግደይ ዘራጽዮን - ጸሃፊ፣ አቶ አስርደው ከበደ - ገንዘብ ያዥ እንዲሁም አቶ ተሻገር ብርሃኔ - ኦዲተር እንዲሆኑ መርጦ መድቧል። የሥራ አመራሩ በበኩሉ ለተለያዩ የሥራ ዘርፎቹ የሚያገለግሉ አባላትን ከምክር ቤቱ ጋር እንዲመድብ መብት ተሰጥቶታል።

ጉባኤው ካጠናቀቃቸው ዋናና አዲስ ነገሮች መካከል የግጭትና ቅራኔ አስወጋጅ ኮሚቴ (የሽማግሌዎች አካል) መፍጠር ነበር። ለዚህም ተግባር የሚመረጡት ሰዎች ከማንኛውም ድርጅት ጋር ያልተያያዙ፣ በመልካም ምግባራቸውና በችሎታቸው ህብረተሰቡ

የሚያምናቸውና የሚያከብራቸው እንዲሆኑ በማሰብ ይህን የሚያሟሉ ከቦታው በተገኙት ሲቋቋም በአጋጣሚ በጉባኤው ያልተገኙትን እንዲጠይቁ ሰዎች ተመድበው አዎንታዊ መልስ ተገኝቷል።

"ድር ቢያብር አንበሳ ያስር"

ኢትዮጵያ በነጻነትና በአንድነት ለዘለዓለም ትኑር!!

ዘረኛውና አገር በታታኙ ሥርዓት በሕዝባዊ ሥርዓት ይተካ!!!

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ

www.dirbiaber.com

ጁን 10. 2012